# <u>ኢሳያስ እያለ ወያነ ጥቃት እንደማይሰነዝር ስብሓት ነጋ አረጋጋጠ</u>

**<u>ጌታቸው ረዳ (Ethiopian Semay አዘጋጅ)</u>**

ከስብሓት ፎቶግራፍ ጋር ተለጥፎ የሚነበበው ጥቅስ የስብሓት ነጋ ንግግር ነው። ምንጩ የተገኘው ለፓርላማ ያደረገው ንግግር ነው ብሎ የለጠፈው በትግራይ ኗሪ የሆነው የድሮ ኢሕአፓ አባል የዛሬ የወያነ ግምባር ቀደም አቀንቃኝ የድሮ የክፍል ጓደኛዬ “ዶ/ር......” የብዕር ስሙ “ኢዛና ዘአክሱም” ነው። ስሙን ላልመጥቀስ የብዕር ስሙን አከብርለታለሁ።




ከንግግሩ የምትረዱት ነገር በርካታ ትርጓሜ መተንትን እንኳ ቢቻልም ፤ ዋናው ፍሬ ነገሩ ሲመነዘር “ኢሳያስ ከሄደ ኤርትራ በቀጥታ ወደ ቀውስ ትገባለች” (የሚለውን አስምሩበት) ስለሆነም ”ኤርትራ ቀውስ ውስጥ እንድትገባ ስለማንፈልግ” የግድ “ኢሳያስ እንዲወገድ አንፈልግም” ወይንም “ኢሳያስ በሚገዛት ኤርትራ ላይ ከባድ ጦርነት ከፍተን ጥቃት ለመሰንዘር አንፈልግም” ነው እያለን ያለው።

በወያኔዎች ትዕዛዝ የሚጓዘው የወያኔዎቹ ተላላኪ ደሳለኝ ሃይለማርያም ደግሞ ፡ ”እንዲህ ብለህ ተናገር” ብለው አለቆቹ ስላዘዙት፤ “ኤርትራ ከትንኮሳዋ ካልታረመች እርምጃ ለመውሰድ እንገደዳለን” ሲል ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ የለፈፈውን የውሸት ቱልቱላውን እውነት መስሎአቸው የወያኔ ቡችሎች ያንኑ እያናፈሱ ሲመረቅኑ አድምጫለሁ።

ኤርትራን በሚመለከት ሁሉ መለስ ዜናዊ እና ስብሐት ነጋ እንዲሁም ሥዩም መስፍን ብቻ ናቸው ወሳኞቹ። ሦስቱም ለኤርትራ አፈቀላጤዎች ናቸው። እውነቱ ግን ፈረሳቸው/በቆሎአቸው ጀሮአችን ላይ እንደሚጮኸው አይደለም። ከእውነታው የራቀ ነው። ወደ ሃቁ የተጠጋ ድምዳሜ ስብሐት በግልጽ አስቀምጦልናል። ሁለት መንግሥት የለም፤ አንድ መንግሥት ነው ያለው። እሱም "ወያኔ" አንጂ 'ሃይለማርያም ደሳለኝ" አይደለም። ወያኔ ማለት ደግሞ "ስብሐት" ማለት ነው። ኤርምያስ ለገሰ የተባለው የድሮ የወያኔ ሚኒስቴርና ዋና መሰሪ ካድሬአቸው የነበረው (ዛሬ የጻፈውን መጽሐፍ በሚገባ የሚደነቅና የሚመሰገን ቢሆንም) ታድያ ታጭቦ ጭቃ እየሆኑብን፤ ተቸግረናል እና፤ ዛሬ ግንቦት ሰባትና ኢሳት ጋር ሆኖ "ለ ሻዕቢያ ገራፊዎች ኢትዮጵያዊያንን አሳልፎ በግርፋት እና በእስር እንዲሰቃዩ ያደረገ፤ የኢሳያስ አፈቀላጤ የነበረው፤ ተሰቃዮቹ "የግንቦቱ ሂትለር" ብለው የጠሩትን አንዳርጋቸው ጽጌን "ማንዴላ" እያለ እየሰየመብን ያለውን (እደግመዋለሁ ኤርምያስ ለገሰ) "ስብሓት ነጋ በወያኔ ስርዓት ኢምንት ቦታ የለውም" ብሎ ቢልም፤ እውነቱ ግን "ስብሓት ነጋ ሥልጣን የተቆጣጠሩት ኤርትራዊያን እና ዓድዋውያን ነገዶች በሙሉ አባትና መሪ መሆኑን እኛ ትግሬዎች ስለምናውቅ፤ ስብሐት አሁንም ተሰሚና እንደ "ስሙ" የወያኔ "አባት"ስለሆነ ፤ ተናገር ተብሎ ከተናገረው ከምስኪኑ ከሃይለማርያም ደሳለኝ የውሸት ማስጠንቀቂያ ይልቅ "ከፈረሱ አፍ" አንደሚባለው "ስብሐት ነጋ" የተናገረውን ሚዛን ስላለው ወያኔ ኤርትራ ድምበር ዘልቆ "ወጣ ገባ" እያለ ቷ! ቷ! እያደረገ ሊየስበረግግው ካልሆነ "ሃይለማርያም" አንደሚለው ሊሆን አይችልም።

ሰሞኑን ሃይለማርያም ደሳለኝ የለፈፈው ከመለስ ዜናዊ ጀምሮ 10 ጊዜ ይሆናል ማስጠንቀቂያ፤ አጸፋ እየተባለ ጆሮአችን ላይ ሲጮሁብን እና ሲያሞኙን የነበሩት። አዲስ አበባን አንደ ባግዳድ፤ እገሌን አንደ እገሌ ወዘተ እየተባለ ፤ኤርትራ ያሰለጠነቻቸው ሰርጎ ገቦች ቦምብ አፈነዱ፤ 'ታክሲ፤አብቶብስ ጋዩ፤ እጅ ከፍንጅ ተያዙ፤ ሲያፈነዱ እጆቻቸውና እግሮቻቸው ተቆርጠው የሚያሳይ ቪዲዮ እና ዜና እያሳየን እንኳ፤ "ሻዕቢያ አላርፍ ካላለ በቀር ባጭር ጊዜ አጸፋ ፤እርምጃ ለመውሰድ  እንገደዳለን....ተብሎ ሰንት ጊዜ ነው በራሱ ፓርላማ ከመሰል ጀምሮ ሲያዋሹን የነበሩት? ምን እርምጃ ወሰደ? ምንም!

ሌላ ቀርቶ፤ ሃይለማርያም እንኳ ባቅሙ ከምላሱ ሸርተት ብላው፤ "ካስፈለገም አስመራ ድረስ ሄጄ ከኢሳያስ ጋር ሰላም ለመፍጠር ዝግጁ ነኝ" እያለ ሲነፋነፍ የነበረውን ስንት ጊዜ ነው የሰማነው። ወያኔ ኢሳያስ እንዳይወድቅ ሚከላከለው ምክንያት አለው። "ኢሳያስ ከሄደ" ኤርትራዊያን በሃሳብ ይከፋፈላሉ። አንዳንዱ ከኢትዮጵያ ጋር ነው የምንሄደው የሚል በጠመንጃ የታፈነው አንደቡትን ለማስተጋባት ዝግጁ የሚያደርግ ቡድንና ተከታይ አንደሚከሰት ወያኔ ስለሚያውቅ 'ኤርትራ" ወደ ኢትዮጵያ እንድትቀላቀል አይፈልግም (ሃገር

ፍቅር ማሕበር አንደገና ከከርሰ መቃብር ወጥቶ "ኲነ ፍስሃ ወሰላም" "ትንሳኤ ሙታን አሰሮ ለሰይጣን" መፈክር እንዳይከሰት ይሰጋል)። ምክንያቱም ዕቅዱ "ወያኔ" ኢትዮጵያ ካልጣመቺው አንቀጽ 39 የተባለውን ፈረሱን ጋልቦ "ወደ ትግራይ ትግርኚው" ውህደት እንደሚሄድ ስለሚያውቅ፤ ያንን ከመሆኑ በፊት "ስብሐት ነጋ" እንደነገረን "ኢሳያስ" ከሄደ "ኤርትራ በቀጥታ ወደ ቀውስ ትገባለች" ወያኔም "ትግራይ ትግርኚው" አደጋ ላይ ይወድቃል ማለት ነው።

የአገር ቤቱ የድሕረ ምርጫው ንዘርት (ሾክ) አልለቅ ስላለኝ አሁንም ሙሉ በሙሉ አላጋገምኩም። ገና ነኝ። እስከዚያው ድረስ ግን ለምርቃታችሁ አንዲሆን የግንቦት ሰባት ዋሾች (ሆቴል ጎሬላ መሪዎቻቸው እና መስኪን ካልቶቻቸው) የወታደራዊ ፋቲክ./ደምብ ልብስ ለብሰው ዋሺንግተን የስፖርት ፌስቲቫል ሲሸሞነሞኑ ነበር ተብሎ ሲነገረኝ "ቡዳሃ" እንደሚለው "ሦስት ነገሮች በምንም መልኩ ልደብቃቸው ብትል አይደበቁም። እነሱም ፀሐይ፤ጨረቃ እና አውነት"።

ይህንን መነጋገሪያ ሰንዘርያለሁ፤ እናንተስ ምን ትላላችሁ?

አመሰግናለሁ
ጌታቸው ረዳ getachre@aol.com